mnvotes.gov

1-877-600-VOTE (8683)

MN Relay Service: 711

secretary.state@state.mn.us

## እንኳን ደስ አሎት፤ እንዲመርጡ ይመዘገባሉ!

የመንጃ ፈቃድ ወይም የክፍለሃገሩን የመታወቅያ ወረቀት ለማውጣት ያስገቡትን ማመልከቻ በመከተል፤ በሚኖሶታ ውስጥ መምረጥ እንዲችሉ ይመዘገባሉ።

### ያሎት ሁለት ምርጫዎች

- **ምንም አያድርጉ፤** ምንም ካላደረጉ ያው ለመምረጥ ተመዝግበዋል ማለት ነው። የአካባቢዎ የአስመራጭ ኮሚቴ መስርያ ቤት፤ የት እንደሚመርጡ ወረዳውን፣ ሰፈሩንና የምርጫ ቦታውን ስም በፖስታ ይልክሎታል።
- **መመዝገብ ካልፈለጉ፤** ለመመዝገብ ካልፈልጉ ወይም ለመምረጥ ብቁ ካልሆኑ (የዚህን ዝርዝር ከበስተጀርባ ይመልከቱ)፤ ይህንን ፎርም ሞልተው፤ ይህ ፎርም ከተላከበት ቀን ጀምሮ በመቁጠር በ20 ቀናት ውስጥ ወደ መስርያ ቤቱ መልሰው ይላኩና ለመምረጥ አይመዘገቡም።

---

## ለመምረጥ መመዝገብ ካልፈለጉ

ለመምረጥ ብቁ ካልሆኑ (ከበስተጀርባ ዝርዝሩን ይመልከቱ) ወይም መመዝገብ ካልፈለጉ፤
ከታች ያለውን ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ፣ ፎርሙን ፈርመው ይመልሱ/ ይላኩ

| | |
|---|---|
| 1 | ☐ በሚኖሶታ ሕግ ቁጥር 201.161 ክፍል 2 (Minn. Stat. 201.161 subd. 2) መሰረት፤ እኔ በሚኖሶታ ለመምረጥ መመዝገብ አልፈልግም፣ ቀደም ብዬም አልመዘገበም። ወይም በፖስታ የተላከልኝ ማስታወሻ ከ 20 ቀናት በላይ ከሆነውና እኔም ለመምረጥ የተመዘገብኩ ከሆነ፤ በሚኖሶታ ሕግ 201.13 ክፍል 4 መሰረት፤ የምርጫ መዝገቤ እንዲነሳልኝ እጠይቃለሁ። |
| 2 | እኔ ይህ ፎርም የተሰጠው ለእኔ መሆኑን በመሃላና በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።<br>ፊርማ፡<br>X |
| 3 | ይህንን ፎርም ስለመመለስ<br>የተሰጠውን ፖስታ፤ ኢሜል ወይም ፋክስ ይጠቀሙበት። |

ለተጨማሪ መረጃ በስተጀርባ ይመልከቱ →

## ሚኖሶታ ውስጥ፤ ለምርጫ ለመምዝገብ ብቁ የሚሆኑት...

- ቀደም ብሎ ለመመዝገብ ዕድሜዎ ቢያንስ 16 ዓመት መሆን አለበት ወይም የመረጡት የምርጫ ዓይነት በሚካሄድበት ዕለት ለመመዝገብ ከፈለጉ ዕድሜዎ ቢያንስ 18 ዓመት መሙላት አለበት።
- የአሜሪካ ዜጋ መሆን አለቦት።
- ከምርጫው ቀን ቢያንስ 20 ቀናት በፊት የሚኖሶታ ተቀማጭ መሆን አለቦት።
- በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዳይመርጡ የታገዱ ወይም የመምረጥ መብትዎ የታገደ መሆን የለቦትም።
- በማንኛውም ፍርድ ቤት ለመምረጥ ብቁ አይደሉም የተባሉ መሆን የለቦትም።
- ወንጄል በመፈጸም እስር ቤት የሚገኙ መሆን የለቦትም።

**ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ማንኛውንም የሚያሟሉ ከሆነ፤ ከበስተጀርባ ያለውን ፎርም በመጠቀም፤ ለመመዝገብ አሻፈረኝ ማለት ይችላሉ።**

## ማወቅ የሚያስፈልግዎ ነገሮች፤

- በማንኛውም ብቁ በሆነ የመንግስት ተቋም ማመልከቻ ያጠናቀቁና፤ የአሜሪካ ዜግነት እንዳላቸው የሚያስረዳ ዶኩመንት ማቅረብ የሚችሉ ሰዎች ካለምንም እክል ወድያውኑ ለመምረጥ መመዝገብ ይችላሉ።
- በኦንላይን ወደ mnvotes.gov/register በመግባት ወይም በአካባቢዎ ባለው የምርጫ ጣብያ ወድያውኑ መመዝገብ ይችላሉ።
- የመመዝገብያው የመጨረሻው ቀን ከምርጫው ቀን 21 ቀናት በፊት ነው። ይሁንና በዛው በራስዎ የምርጫ ጣብያ ውስጥ፤ በምርጫው ቀንም ሊመዘገቡ ይችላሉ። ለመመዝገብ ምን ዶኩመንቶችን ወይም መታወቅያ ወረቀቶችን ማምጣት እንደሚያስፈልጎ ለማወቅ ኦንላይን ወደ *mnvotes.gov* ገብተው ይጎብኙ።
- እንዳንድ ሲመዘገቡ የሰጧቸው መረጃዎች፤ ለምርጫ፤ ለፖለቲካ ወይም ለህግ ማስፈጸምያ ስራ ወይም ጁሪ ወይም ፈራጆችን ለመምረጥ የሚካሄድ ስራ ሲሆን በአደባባይ ይወጣሉ፤ ከህዝብ እይታም የሚደበቁ አይሆንም። ይህ ነገር ከወጣ ለእኔ ጥሩ አይደለም የሚል ስጋት ካለቦት እርሶ የሚገኙበትን አድራሻ የሚመለክት መረጃ በሚስጢር እንዲያዝ ማድረግ ይችላሉ፤ ስለዚሁ ጉዳይ በበለጠ ለመረዳት ከፈለጉ በስልክ ቁጥር 1-877-600-8683 ይደውሉ።

**የት እንደሚመርጡ፤ በአካባቢው በሌሉበት እንዴት መምረጥ እንደሚችሉ (absentee ballots)፣ የናሙና ምርጫዎችን (sample ballots) ለማየት፣ የተመዘገቡበትን ሁኔታ ለማሻሻል ወይም ወቅታዊ ለማድረግ እና ወዘተ... ለማወቅ ሲፈልጉ ኦንላይን ወደ Visit mnvotes.gov በመግባት ይረዱ።**

## የመረጮች ምዝገባን በተመለከተ በሌሎች ቋንቋዎች የቀረበ

ይህንን ከታች የሚታየውን በመቅዳት ወይም በኦንላይን ወደ mnvotes.gov/register በመግባት ይህንን መረጃ በእነዚህ በተመዘገቡት ቋንቋዎች ተከታተሉ።

Español Soomaali Русский ພາສາລາວ ខ្មែរ

Hmoob Tiếng Việt 中文 Oromo አማርኛ

ሰላሎት አማራጮች ወደ ሌላው ገጽ ያምሩ →